**በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለከተማ የ2018 ዓ.ም የ6ኛ ክፍል የግብረገ ሞዴል ፈተና**

1. ሀላፊት ማለት ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. የፈለጉትን ነገር ብቻ ማድረግ ለ. የሚጠበቅብንን ተግባርና ግዴታን መወጣት

ሐ. ስራን ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት መ. ከቅጣት ለማምለጥ መሞከር

2. ሀላፊነትን መወጣት ሲባል ምን ማለት ነው ?

ሀ.የሚጠበቅብንን ተግባር በአግባቡ ማሟላት ለ.ለምናደርገው ነገር ተጠያቂ አለመሆን

ሐ.እራሳችንን መጠበቅ መ. ስልጣን መያዝ

3. ከሚከተሉት ውስጥ ከሀላፊነት አይነቶች ውስጥ አይመደብም

ሀ. የግለሰብ ሀላፊት ለ. የቤተሰብ ሀላፊነት

ሐ. ሀገራዊ ሀላፊነት መ. የሌሎችን ስሜት ያለማክበር

4.ከግብረገባዊ ሀላፊነት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው ?

ሀ.ቃልን መጠበቅ ለ. የሌሎችን ችግር አለመረዳት

ሐ. አባካኝነት መ. ለ እና ሐ

5. ንቁ ዜጋ ሲባል ምን ማለት ነዉ?

ሀ. ዘመናዊ ፋሽኖችን የሚከተል ማለት ነው

ለ. በአካባቢው ማህበረሰብ ወይም በሀገር ደረጃ የነቃ ተሳትፎ የሚያደርግ

LIVEWORKSHEETS

ሐ.ብልጣብልጥ የሆነ

መ. ተምሮ የጨረሰና ስልጣን ያለው

6. _______ በግለሰብ ወይም በዜጎች ለሀገራቸው የሚከፍሉት የውዴታ ግዴታ ነው

ሀ. ሙስና ለ. የትራፊክ ቅጣት ሐ. ግብር መ. ቁጠባ

7. ጠንክሮ መስራት ወይም ታታሪነት ምንድን ነው?

ሀ.ጊዜንና ጉልበትን ስራ ላይ ማዋል ለ. ጊዜን ማባከን ነው

ሐ. የመስራት ፍላጎት ወይም ተነሳሽነት ማጣት መ. ሳይሰሩ የመብላት ፍላጎት

8. ከሚከተሉት አንዱ ጠንካራ የስራ ባህል አስፈላጊነትን ይገልፃል

ሀ. የሚሰሩትን ስራ በግዴለሽነት ማከናወን ለ. የሀገር ፍቅር ስሜት ያለመኖር

ሐ. የተሻለ ኑሮ ለመኖር መ. በድህነት መኖር

9. የታታሪ ሰዎች ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ጊዜን በአግባቡ መጠቀም ለ. ስራቸዉን በፕሮግራም ማከናወን

ሐ. በሰዎች ላይ ጥገኛ መሆን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

10. አንድ ታታሪ ሰው ካጋጠመው ውድቀት ምን ይማራል?

ሀ. ውድቀቱን እንደትልቅ ስህተት አይቶ ይደበቃል

ለ.ተስፋ ቆርጦ ስራውን ያቆማል

LIVEWORKSHEETS

ሐ.ዕድሉንና ሌሎችን ይረግማል

መ.ከስህተቱ ተምሮ ለተሻለ ውጤት እንደገና ይነሳል

11. ንባብ ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ. ፊደላትን በቃል መጥራት ብቻ ነዉ   ለ.በጽሁፍ የሰፈሩት መልዕክቶች መረዳት

ሐ.መፅሐፍን ሳይረዱ ገለጦ ማየት   መ.የተሰማንን ሀሳብ በወረቀት ላይ ማስፈር

12. አንድ የተወሰነን መረጃ ብቻ ለመፈለግ ሲባል በፍጥነት ማንበብ ነው?

ሀ. የአሰሳ ንባብ   ለ. የመቃኘት ንባብ

ሐ. የሀረግ ንባብ   መ.አላማ ያለው ንባብ

13. _______ የፅሑፍን አጠቃላይ ሀሳብ ለማግኘት ሲባል በፍጥነት ማንበብ ነው?

ሀ.የመረጃ ቃላት   ለ.አላማ ያለው ንባብ

ሐ. የሀረግ ንባብ   መ. የአሰሳ ንባብ

14. ግብረገባዊ ውሳኔ ከሌሎች ውሳኔዎች የሚለየው በምንድነው?

ሀ. በግል ፍላጎት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስለሆነ

ለ.በፍትሀዊነት፣በሰብአዊ መብት እሴቶች ላይ ስለሚመሰረት

ሐ. በሕግ ቅጣት ላይ ብቻ ትኩረት ስለሚያደርግ

መ. ፈጣን እና ያለጥልቅ ትንታኔ የሚወሰን ስለሆነ

LIVEWORKSHEETS

15. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገባዊ ውሳኔ ችሎታ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. አሳቢነት ለ. ምክንያታዊነት

ሐ. ግትርነት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

16. ምክንያታዊ ውሳኔ ለመወሰን ከምንከተለው ቅደም ተከተል ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ.ችግሩን መለየት ለ. አነቃቂ አማራጮችን መዘርዘር

ሐ. ሊከሰቱ የሚችሉ ውጤቶችን መለየት መ. የራስን ፍላጎት በሌሎች ላይ መጫን

17. ግብረገባዊ ውሳኔ ለምን ያስፈልጋል ?

ሀ. ችግሮችን ብልሀት በተሞላበት ዘዴ ለመፍታት ያስችላል

ለ. በሰዎች መካከል መተማመን እንዳይኖር ለማድረግ

ሐ. የወደፊት ሕይወት የተሳካና የተቃና ለማድረግ

መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

18. ማህበራዊ ትስስርና ሰላምን ለማጠናከር የግብረገባዊ ውሳኔ አስፈላጊነት በምን ይገለፃል?

ሀ. በሰዎች መካከል ፍትህና እኩልነት እንዲሰፍን በማድረግ

ለ. ሁሉም ሰው የራሱን ፍላጎት ብቻ እንዲያስቀድም በማበረታታት

ሐ. ባለስልጣናትን ብቻ በመታዘዝ

መ. ጥፋተኞችን በይፋ ባለመጠየቅ

LIVEWORKSHEETS

19.የግብረገባዊ ውሳኔ ተግዳሮት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ.የተገደበ ምክንያታዊነት ለ.ለራስ የሚሰጥ ግምት

ሐ. የበዛ ቁርጠኝነት መ.እርስ በእርስ መረዳዳት

20. የአቻ ግፊት በግብረገባዊ ውሳኔ ላይ ተግዳሮት የሚሆነው ለምንድን ነው ?

ሀ. ግለሰቦች የራሳቸውን የሞራል እሴት ትተው የጓደኞቻቸውን ፍላጎት እንዲከተሉ ስለሚያስገድድ

ለ. ሁል ጊዜ ትክክለኛ ውሳኔ ላይ ለመድረስ ስለሚረዳ

ሐ. የግል ነፃነትን ስለሚያበረታታ

መ. ውሳኔዎች በምክንያት ላይ ብቻ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ስለሚረዳ

21. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ምሉዕነትን በይበልጥ የሚገልፀው የቱ ነው ?

ሀ. ሰዎች ስለ ነገሮች ባላቸው ግላዊ እምነት ተለዋዋጭ አቋም ሲያሳዩ

ለ. ሰዎች የራሳቸውን መሠረታዊ እምነት በሌሎች ሰዎች ላይ መጫን ሲችሉ

ሐ. ሰዎች ስለ ነገሮች ባላቸው ግላዊ እምነት ቋሚ አመለካከት ሲያንፀባርቁ

መ. ሰዎች የሌሎች ሰዎችን መሠረታዊ እምነትና ድርጊት ሲቀበሉና ሲተገብሩ

22. የግብረገብ ምሉዕነት መገለጫ የሆነው የቱ ነው?

ሀ.ግዴለሽነት ለ. ተለዋዋጭነት ሐ. ግትርነት መ. ኢ _ ተለዋዋጭነት

LIVEWORKSHEETS

23. አቶ አበበ ልጆቻቸውን ስለ መልካምነት፣ጠንክሮ ስለመስራት፣ስለ ሀገር ፍቅር ይመክሯቸዋል።ልጆቹም የአባታቸውን ምክር ይሰማሉ። ነገር ግን አቶ አበበ በስራ ቦታቸው ከሰዎች ጋር የማይስማሙ፣ ግብር በአግባቡ የማይከፍሉ ሰው ናቸው። የአቶ አበበ ባህሪ _____ ነዉ ።

ሀ.ወጥ ባህሪ ለ.ተለዋዋጭ ባህሪ ሐ.ስለ ሌሎች ማሰብ መ. ኢ_ተለዋዋጭ ባህሪ

24. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገብ ምሉዕነት ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ. ችግሮችን በብቃት የመፍታት አቅምን ያሳጣል

ለ. መጥፎ ተግባራትን የሚያጋልጡ ግለሰቦችን ማሳነስ

ሐ. በራሳቸው የሚተማመኑ ጠንካራ የስራ ባህል ያለው ማህበረሰብ መፍጠር

መ. በቀላሉ የገቡትን ቃል የሚያፈርሱ ግለሰቦች መበርከት

25. ከሚከተሉት አንዱ ምሉዕነት የተላበሱ ግለሰቦች ባህሪ አይደለም

ሀ. ሌሎች የተሳሳተ ድርጊት ሲፈፅሙ በዝምታ አይመለከትም

ለ.የሰሩትን ስህት በራሳቸው መቀበል ይችላሉ

ሐ. ውስጣዊ እምነታቸውን በማይገልፅ ተግባር ላይ ይሳተፋሉ

መ.የሰሯቸውን ስራዎች በአግባቡ ይገመግማሉ

26. የግብረገብ ምሉዕነት አለመኖር የሚያስከትለው ችግር የቱ ነው ?

ሀ. በራስ መተማመን ችሎታን ይጨምራል ለ.ጠንካራ ማህበረሰብ መፍጠር

LIVEWORKSHEETS

ሐ.በሰዎች ዘንድ እምነት ማጣት　　　　　　　　　　መ.የሌሎች ሰዎችን ሚስጥር መጠበቅ

27.የሕጎችን ምንነት በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነዉ ?

ሀ. የዜጎችን መብትና ግዴታ የሚያሳውቁ መመሪያዎች ናቸው

ለ.ጥቂት ዜጎች ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነምግባር ደንቦች ናቸው

ሐ.በፍጥነት ተለዋዋጭና ወጥነት የሌላቸው መመሪያዎች ናቸው

መ.ከዜጎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት የለውም

28. ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ መገዛት አስፈላጊነት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?

ሀ.ሰላምን ለማስፈን　　　　　　　　　　ለ. ኢ_ኢፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር

ሐ.ሙሉ ነፃነት ለማግኘት　　　　　　　　　　መ.የዜጎችን ፍላጎት ለመጠበቅ

29. ለህግ ተገዥ ከሆኑ ሰዎች ባህሪ ውስጥ የማይካትተው የቱ ነው ?

ሀ.መብታቸውን የሚያስከብሩ እና የሰዎችን መብት የሚጥሱ ናቸዉ

ለ.ቋሚ የሆነ ባህሪ አላቸው

ሐ.ሰላምን ያስጠብቃሉ

መ.መብትና ግዴታቸውን ያውቃሉ

30.ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዥ አለመሆን የሚያስከትለው አሉታዊ ውጤት የቱ ነው?

ሀ.የሰብአዊ መብት መከበር　　　　　　　　　　ለ. የሰላም እጦት

LIVEWORKSHEETS

ሐ. ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል　　　　　መ. ሙሉ ነፃነት ማግኘት

31. ሉዓላዊነትን በትክክል የሚገልጸው የቱ ነው ?

ሀ.ከሌሎች ሀገሮች ጋር ትስስር መፍጠር　　　　　ለ.ከውጭ እርዳታ መቀበል

ሐ. ከጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ ራስን ማስተዳደር　　　　　መ.ብዙ ሀብት ማከማቸት

32. ህግ አክባሪዎች ለህግ ያላቸው አመለካከት በምን ይገለፃል?

ሀ. ቅጣትን ስለሚፈሩ ብቻ ህግን ያከብራሉ

ለ. ህግ የሰላምና የስርአት መሰረት መሆኑን አምነው ይቀበላሉ

ሐ.የሚጠበቅባቸውን ህግ ብቻ መርጠው ያከብራሉ

መ. ህግን መጣስ እንደ ጀግንነት ይቆጥራሉ

33. በአንድ ሀገር ውስጥ ህግ ካልተከበረ በኢኮኖሚው ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ ይኖረዋል ?

ሀ.ቱሪስቶች በብዛት መምጣት ይችላሉ　　　　　ለ. የንግድ ስርዓቱ ይዘምናል

ሐ.ስርቆት፣ሙስና ስለሚኖር ልማት ይቆማል　　　　　መ. የኑሮ ውድነት ይቀንሳል

34.መልካም ባህሪ ሲባል ምን ማለት ነዉ ?

ሀ. በሰዎች ፊት ጥሩ መስሎ መታየት ነው

ለ.በአንድ ግለሰብ አስተሳሰብ ስሜትና ተግባር ውስጥ የሚንፀባረቅ ቅንነትና ስነምግባር

ሐ.ሀብታምና ተደማጭ መሆን

LIVEWORKSHEETS

መ.የራስን ፍላጎት ለማርካት ሌሎችን መጠቀም

35. ከሚከተሉት ውስጥ መልካም ባህሪ የተላበሰ ሰው ባህሪ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ.ራስ ወዳድነት ለ. ማጭበርበር ሐ.ደግነት መ.ፍርሃት

36.ከሚከተሉት አንዱ የመልካም ባህሪ ባለቤት መሆን ጠቀሜታ ነው

ሀ.በሰዎች ዘንድ አመኔታን ማግኘት ለ.የመልካም ግንኙነት መጓደል

ሐ.ከሌሎች ሰዎች ጋር መጋጨት መ.የጓደኛ እጦት

37.አላስፈላጊ ውስጣዊ ግፊትን፣ስሜትንና ምኞትን የመቆጣጠር ብቃት ነዉ

ሀ.ታማኝነት ለ.ተጠያቂነት ሐ. ራስን መቆጣጠር መ.ሉዐላዊነት

38.ከማህበረሰብ እሴቶች ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ?

ሀ.ሰላምታ መለዋወጥ ለ.ሰዎችን በእኩል አይን አለማየት

ሐ. ስርዓት ያለው አለባበስ መ.እንግዳ ተቀባይነት

39.ከሚከተሉት ውስጥ መልካም ባህሪ ላይ አስተዋጽኦ የሌለው የቱ ነወ?

ሀ.ቤተሰብ ለ.ምርጫ ሐ. ጊዜ መ. ሙስና

40.መልካም ባህሪ አለመኖር ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው ?

ሀ.እውነትን መናገር ለ.ያልተገባ አለባበስ

ሐ.የፈተና ኩረጃ መ.የራስን ንብረት በአግባቡ አለመያዝ

LIVEWORKSHEETS